የአዲስ ገቢዎች ጉዳይ ሚኒስተር ወ/ሮ ፕኒና ታምኖ እሸቴ ለአዲስ ገቢዎች ኮሮናን ምክንያት ያደረገ ልዩ የገንዘብ ድጎማ እንደሚያደርጉ አብስረዋል።
በዚህ ዓመት ወደ እስራኤል ለገቡ በሺዎች ለሚቆጠሩ አዲስ ገቢዎ የኮሮናን የኢኮኖሚ ቀውስ ምክንየት በማድር በቢቱዋህ ለኡሚ ድጋፍ ለማይደረግላቸው 500 ሸቄል እንዲቀበሉ በዛሬው እለት የአዲስ ገቢዎች ጉዳይ ሚኒስተር ፕኒና ታምኖ እሸቴ ውሳኔ አስተላልፈዋል።
የአዲስ ገቢዎች ጉዳይ ሚኒስተር በአለፉት ሳምንታት ብዙ ትግል አድርገዋል። ምክንያቱም በዚህ ዓመት ውስጥ ወደ እስራኤል የመጡ አዲስ ገቢዎች በኮሮና ምክንያት የኢኮኖሚ ችግር ቢድርስባቸውም በመንግስት ወሳኔ መሰረት እንደማንኛውም ዜጋ በቢቱዋህ ለኡሚ እርዳታ ከመቀበል በመገለላቸው የደረሰባቸውን ችግር ለመቅረፍ ሚኒስተሯ ትልቅ ትግል አድርገዋል። ስለዚህ አዲስ ገቢዎችም እንደማንኛውም ነባር እስራኤላዊያን ቤተሰብ የገንዘብ እርዳታ እዲቀበሉ ውሳኔ ላይ ተደርሷል።
የአዲስ ገቢዎች ጉዳይ ሚኒስተር ወ/ሮ ፕኒና ታምኖ እሸቴ እንዳሉት "የሚያሳዝነው ነገር አዲስ ገቢዎች በኮሮና ምክንያት ከሚጎዱ ማህበረሰቦች ይመጀመሪያዎ መሆናቸው ነው። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከነባሩ ህብረተሰብ ጋር ሲወዳደር ስራ የሌላቸው የአዲስ ገቢዎች ቁጥር በጣም ከፍተኛ ነው። ይህ ደግሞ አዲስ ገቢዎች ከሚቋቋሟቸው ሌሎች ችግሮች ጋር በመደመር ህይወታቸው የከበደ እንዲሆን ያደርጋል። ማንኛውም እርዳታ ለእነርሱ ያለ ጥርጥር አስፈላጊ ነው፣ እኔ የአዲስ ገቢዎችን ህይወት በማንኛውም ዘርፍ ጥሩና ፈተናዎች ያልበዙበት እንዲሆን ጥረቴን እቀጥልለሁ። ቴንነታቸውን በመጠበቅም ሆነ የኢኮኖሚ ደረጃቸውን በማሻሻልም።"
ከዚህ በተጨማሪ የአዲስ ገቢዎች ጉዳይ ሚኒስተር ወ/ሮ ፕኒና ታምኖ እሸቴ ለሀገር ውስጥ ደህንነት ሚኒስተር አሚር ኦሃና እና ለህግና ፍትህ ሚኒስተር አቪ ኒሳንኮሬን በኮሮና ወቅት በስር ቤቶችና በምርመራ ክፍሎች ጠያቂዎችን እና የህግ ጠበቃዎችን የሚከለክለውን ህግ በአስቸኳይ እንዲያስተካክሉ ጥሪ አድርገዋል። እንደ ህጉ የመጀመሪያ ትንታኔ መሰረት የታሰሩና የተጠረጠሩ ወንጀለኞች ከህግ ጠበቃ ጋር በቴክኖሎጂ በኩል ምክር ማድረግ እንደሚችሉ ነው። ይህም በስር ቤቶች የኮሮና ቫይረስን መዛመት ለማቆም እንዲቻል ነው። እንደ የአዲስ ገቢዎች ጉዳይ ሚኒስተር ወ/ሮ ፕኒና ታምኖ እሸቴ አባባል የመጀመሪያ የህጉ ይዘት መሰረት የሒብሩ ቋንቋን ለማይናገሩ አዲስ ገቢዎች መፍትሄ የለም። ስለዚህ የአዲስ ገቢዎችን መሰረታዊ መብት ለመጠበቅ በአስተርጓሚ የታገዘ የምክር አገልግሎት ሊሰጣቸው ይገባል። ህጉ በቀርብ ቀን በመግስት የሚፀድ ይሆናል።